የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን · ADDIS ABABA CITY ROADS AUTHORITY ·

# መንገድ ምረቃ

**ልዩ ዕትም**



2017 ዓ.ም

**የተሻለ መንገድ ለተሻለች አዲስ አበባ!**
**Better roads for better Addis!**

# የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን

## ራዕይ (Vission)

በ2022 ዓ.ም ሁሉን አቀፍ የመንገድ መሰረት ልማት በማቅረብ አዲስ አበባ ከተማን በመንገድ ዘርፍ ከአፍሪካ 5 ተመራጭ ዋና ከተሞች አንዷ ማድረግ ነው፡፡

## ተልዕኮ (Mission)

በአዲስ አበባ ከተማ የመንገድ ግንባታ፣ ጥገና እንዲሁም የማስተዳደር ስራን ውጤታማ እና ወጪ ቆጣቢ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ጥራቱና ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አስተማማኝ፣ ለአከባቢ ተስማሚ እና ዘላቂነት ያለው ሁሉን አቀፍ የመንገድ መሰረተልማት በማቅረብ የህብረተሰቡን እርካታ ማሳደግ፣

## እሴቶች (Values)

1. ጥራትና ወጪ ቆጣቢነት (Quality and Low Cost)
2. ቅድሚያ ለደህንነት (Safety)
3. ዘላቂነት/Sustainability/
4. ፍትሃዊነት (Impartiality)
5. ሙያዊነት/ Proffessionalism
6. የላቀ አገልግሎት መስጠት (/Service Exellecence/
7. ለለውጥ ዝግጁነት (Readiness for Change)
8. ግልፀኝነት (Transparency)
9. ተጠያቂነት (Accountability)

# መልዕክት



**ሙህዲን ረሻድ (ኢንጂነር)**
**ዋና ዳይሬክተር**

በቅድሚያ እንኳን ለ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ዙር የመንገድ ምረቃ ሥነ-ስርዓት በሠላም አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ።

የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን ባለፉት ዓመታት ባካሄደው መጠነ-ሰፊ የመንገድ ግንባታ እንቅስቃሴ፣ የከተማዋን ነባር መንገዶች ደረጃ ከማሻሻል በተጨማሪ፣ በርካታ አዳዲስ መንገዶችን በጥራት እና በፍጥነት በመገንባት የመዲናችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት እንዲፋጠን ጉልህ ድርሻ ሲያበረክት ቆይቷል።

ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ የከተማዋ የመንገድ ኔት-ወርክ ደህንነቱ ተጠብቆ የተቀላጠፈ የትራፊክ ፍሰት እንዲኖር ለማስቻል በየጊዜው መደበኛ እና ወቅታዊ የመንገድ ጥገና ሥራዎችን ከማከናወን ጎን ለጎን፤ በተለያዩ የከተማዋ ማዕዘናት ሲገነባቸው ከነበሩ የመንገድ ፕሮጀክቶች መካከል 12 የመንገድ መሠረተ-ልማቶችን እና የተቋሙን ማዕከላዊ ጋራዥ ግንባታ አጠናቆ እነሆ ለምረቃ አብቅቷል። በዚህ የምረቃ ሥነ-ስርዓት ከተካተቱት ግዙፍ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች መካከል ሁለቱ ማለትም የቃሊቲ - ቱሉ ዲምቱ እና የቃሊቲ - ቅሊንጦ የመንገድ ፕሮጀክቶች በድምሩ 22 ኪሎ ሜትር ርቀት እና 50 ሜትር የጎን ስፋት የሚሸፍኑ ሲሆን፤ ቀደም ሲል በደቡባዊው የከተማዋ የወጪ - ገቢ ኮሪደር ላይ ይፈጠር የነበረውን የትራፊክ ፍሰት ጫና በከፍተኛ ደረጃ የሚያቃልሉ ናቸው።

በሌላም በኩል በኮዬ ፈቼ እና በቱሉ ዲምቱ አካባቢ የሚገኙ ነዋሪዎች በአጭር ርቀት ወደ መሐል ከተማ እንዲደርሱ እነዚህ ሁለት ግዙፍ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያላቸው ከመሆኑም ባሻገር፣ የቃሊቲ - ቂሊንጦ መንገድ በአካባቢው ለሚገኘው የኢንዱስትሪ መንደር እንቅስቃሴ መሳለጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል።

በተመሣሣይም የቱሉ ዲምቱ የጋራ መኖሪያ መንደሮች መቃረቢያ መንገድ፣ በአጉስታ- ወይራ፣ በጀሞ፣ በበሻሌ ኮንዶሚኒየም፣ በቂርቆስ - ቡልጋሪያ፣ በ22 ማዞሪያ - ሾላ አቅጣጫና አካባቢዎች በባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ የራስ ኃይል አቅም እና በኮንትራት የተገነቡት ሌሎች 10 የመንገድ ፕሮጀክቶች፣ በየአካባቢው ያለውን የመንገድ ኔትወርክ ይበልጥ በማስተሳሰር የተሻለ የትራፊክ ፍሰት እንዲኖር ታሳቢ ተደርገው የተገነቡ ናቸው።

የባለሥልጣን መስሪያ ቤቱን ማዕከላዊ ጋራዥ ጨምሮ በአጠቃላይ ከ6 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ የተገነቡት እና 33 ነጥብ 6 ኪሎ ሜትር ርቀት የሚሸፍኑት እነዚህ ፕሮጀክቶች የከተማዋን የመንገድ ሽፋን ከማሳደጋቸውም ሌላ የአዲስ አበባን ገፅታ በማሻሻል በኩል ተጨባጭ ለውጥ አምጥተዋል።

ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ በቀጣይም እያካሄደ የሚገኘውን የመንገድ መሰረተ-ልማት የማስፋፋት ዐብይ ተልዕኮ አጠናክሮ በማስቀጠል የህብረተሰቡን የመንገድ ዘርፍ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በትጋት እንደሚሰራ በዚህ አጋጣሚ ላረጋግጥ እወዳለሁ።

በመሆኑም የመንገድ መሠረተ-ልማቱ ዋነኛ ባለቤት የሆነው መላው የከተማችን ነዋሪ፣ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የጋራ መጠቀሚያ የሆነውን የመንገድ ሃብት በአግባቡ በመጠቀም፣ በጋራ በመጠበቅ እና በመንከባከብ የከተማዋ መንገዶች ረጅም ጊዜ አገልግሎት እንዲሰጡ የበኩሉን አዎንታዊ ሚና እንዲወጣ በራሴ እና በባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ስም ጥሪ አቀርባለሁ።

አመሰግናለሁ !

## መግቢያ

## የዘመናዊ መንገዶች ልማት ለውብ የከተማ ገጽታ እና ለቀልጣፋ የትራፊክ ፍሰት

መንገድ፤ የአንድን አካባቢ ብሎም የከተማና የሀገርን ሁለንተናዊ እድገት ለማፋጠን ቁልፍ ድርሻ ከሚያበረክቱ መሠረተ-ልማቶች መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነው። ሁሉም ዓይነት መሠረተ-ልማቶች ለተቀናጀና ሁሉን አቀፍ ዘመናዊ እድገት አስፈላጊ መሆናቸው አጠያያቂ ባይሆንም፤ ሌሎች የመሠረተ-ልማት አቅርቦቶች በፍጥነትና በስፋት እንዲዳረሱ የመንገድ ግንባታ በእጅጉ ያስፈልጋል።

በመሆኑም በመሠረተ-ልማት መስክ የመንገድ ግንባታ ልዩ ትኩረት እንዲሰጠውና ቀዳሚ የትኩረት አቅጣጫ እንዲሆን ምክንያት ሆኗል።

ከዚህ እውነታ በመነሳት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማዋ መጠነ ሰፊ የመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታ እንዲከናወን ከማድረግ ጎን ለጎን፣ የከተማዋ ነባር መንገዶች አካታችና ተደራሽ በሆነ መልኩ ዘመናዊ ሆነው እንዲሻሻሉ እያደረገ ይገኛል።

የመዲናዋን የመንገድ መሠረተ-ልማት የመገንባት፣ የመጠገን እና የማስተዳደር ኃላፊነትና ተልዕኮ የተሰጠው የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን፤ ባለፉት 7 ዓመታት ባከናወናቸው የመንገድ ዘርፍ እንቅስቃሴዎች ብዛት ያላቸው የአስፋልት፣ የኮብል፣ የጠጠር እና የእግረኛ መንገዶች ግንባታ በማካሄድ ለአገልግሎት ማብቃቱ ይታወሳል።

አዲስ አበባ ስምና ግብሯን የሚመጥን፣ የዘመናዊ መንገዶች ባለቤት ትሆን ዘንድ፤ ባለሥልጣን መስሪያቤቱ በዓይነትና ይዘታቸው የተሻሻሉ የመንገድ ዲዛይኖችን አዘጋጅቶ ገቢራዊ በማድረግ ያስመዘገባቸው ለውጦች፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ከተማ የመፍጠር ፍላጎትን ታላሚ ያደረገው የከተማ አስተዳደሩን ግብ ከማሳካት አንፃር ተስፋ ሰጪ ውጤት እያሳየ ይገኛል።

በየዓመቱ የግንባታ ሥራቸው ተጠናቆ ወደ መንገድ ኔት ወርክ የገቡት የከተማዋ መንገዶች፤ የአዲስ አበባን የቀድሞ የተጎሳቆለ ገፅታ ከመቀየር ባለፈ፣ የትራፊክ ፍሰቱ እንዲቀላጠፍ፣ በየአካባቢው ያለው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት እንዲጎለብት እና ዘመናዊ የከተማ ቅርፅ እንዲፈጠር የላቀ ድርሻ እያበረከቱ መሆኑ የአደባባይ እውነታ ነው።

እንደ አለፉት ዓመታት ሁሉ፤ በዚህ ዓመትም በአጠቃላይ ከ6 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገባቸው 12 የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በራስ ኃይል እና በኮንትራት ተገንብተው ለምረቃ በቅተዋል። በአጠቃላይ 33.6 ኪሎ ሜትር ርዝመትና በአማካይ ከ10 - 50 ሜትር የጎን ስፋት ካላቸው ከእነዚህ 12 የመንገድ ፕሮጀክቶች በተጨማሪ፤ የተቋሙን የመፈፀም አቅም በማጠናከር በኩል ከፍተኛ ድርሻ ያለውን የተቋሙን የመሣሪያዎች አስተዳደርና ጥገና ማዕከል ለማዘመን ከ530 ሚሊየን ብር በላይ በሆነ ወጪ በቃሊቲ አካባቢ የተገነባው የባለሥልጣን መስሪያቤቱ ማዕከላዊ ጋራዥ ሌላው የዚህ ምረቃ ሥነ-ስርዓት አካል ነው።

በ2017 በጀት ዓመት የምረቃ ሥነ-ስርዓት ለአገልግሎት ክፍት የተደረጉ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ዝርዝር እንዲመለከቱ ከዚህ እንደሚከተለው አቅርበናል።

# 1. የቃሊቲ-ቂሊንጦ መንገድ




መጋቢት 2009 ዓም ግንባታው የተጀመረው የቃሊቲ -ቂሊንጦ መንገድ 10.5 ኪሎ ሜትር ርዝመትና 50 ሜትር የጎን ስፋት ያለው ሲሆን 5 ድልድዮችን አካትቶ የተገነባ መንገድ ነው።

ከድልድዮቹ መካከል ሁለቱ ወንዝ ተሻጋሪ ድልድዮች ሲሆኑ ሶስቱ ደግሞ መንገድ ተሻጋሪ ድልድዮች ናቸው።

- የመጀመሪያው ድልድይ በቡልቡላ ወንዝ ላይ የተገነባው እና 175 ሜትር ርዝመት እና በግራና በቀኝ መተላለፊያው በኩል 34 ሜትር የጎን ስፋት ያለው ነው።
- የቡልቡላ ወንዝን አቋርጦ የሚያልፈው ይህ ድልድይ ከታች ወደ ላይ 30 ሜትር የሚረዝም ከፍታም አለው።
- ሁለተኛው ወንዝ ተሻጋሪ ድልድይ በትልቁ የአቃቂ ወንዝ ላይ የተገነባው ሲሆን 325 ሜትር ርዝመት አለው።
- የትልቁ አቃቂ ወንዝ ድልድይ 42 ሜትር ከፍታ ያለው ሲሆን፣ እያንዳንዱ የድልድዩ ምሰሶ ከመሬት በታች እስከ 30 ሜትር በሚደርስ ጥልቀት መሠረት የተገነባ ነው።





ቀሪዎቹ ሶስት የመንገድ ተሻጋሪ ድልድዮች በፕሮጀክቱ የተለያየ ስፍራዎች ላይ የተገነቡ ሲሆን፣ ቂሊንጦ አካባቢ በሚገኘው ኢንዱስትሪ ፓርክ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ላይ ተሻግረው የሚያልፉ እና ወደ ውጪኛው የቀለበት መንገድ የሚያሻግሩ ናቸው።

2 ቢሊየን 264 ሚሊየን 711 ሺህ 627ብር ወጪ የሆነበትን ይህ መንገድ የገነባው የቻይና ኮንስትራክሽን ኮሙኒኬሽን ካምፓኒ ሲሆን ሀይ ዌይ ኢንጂነርስ እና ኮንሰልታንት ፕሮጀክቱን በማማከር ተሳትፈዋል።

ይህ መንገድ የከተማዋን የኢንዱስትሪ ፓርክ በመንገድ መሠረተ-ልማት የሚያስተሳስርና በቱሉዲምቱ የክፍያ መንገድ አቅጣጫ ወደ ከተማዋ ለሚገቡና ለሚመጡ ተሽከርካሪዎች የወጪ ገቢ ኮሪዶር ሆኖ የሚያገለግል ዋና መንገድ በመሆኑ በቃሊቲ ቱሉ ዲምቱ መንገድ ላይ የሚኖረውን የትራፊክ ጫና እንደሚያቃልል ይታመናል።

በተጨማሪም የቂሊንጦ ኢንደስትሪ ፓርክን ጨምሮ ለሌሎች ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ዕቃዎችን በፍጥነትለማቅረብና ምርትና አገልግሎቶችን ለአካባቢው ማህበረሰብ ለማድረስ ያስችላል።

## 2.የቃሊቲ አደባባይ ቱሉ ዲምቱ መንገድ



የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን ካስገነባቸው ትላልቅ የመንገድ ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ የሆነው የቃሊቲ አደባባይ ቱሉ ዲምቱ መንገድ ዋነኛው የወጪ እና ገቢ ዕቃዎች መተላለፊያ መንገድ በመሆኑ ለከተማዋ ብሎም ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት መፋጠን ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ይታመናል።

በሚያዚያ ወር 2009 ዓ.ም የመሰረተ ድንጋይ የተቀመጠለት ይህ የመንገድ ፕሮጀክት ከወሰን ማስከበር እና ከብድር አከፋፈል ጋር በገጠሙት ሁለት መሰረታዊ ችግሮች ምክንያት በሚፈለገው ፍጥነት የግንባታ ስራው ሳይከናወን መቆየቱ ይታወሳል።



የፕሮጀክቱን ግንባታ ሂደት ያጓተቱት ችግሮች በፍጥነት እንዲፈቱ የከተማ አስተዳደሩ ባደረገው ድጋፍና ክትትል መሰረት ቀሪ የግንባታ ስራዎች ተጠናቀው መንገዱ ለአገልግሎት መብቃት ችሏል።

11 ነጥብ2 ኪ.ሜትር ርዝመትና 3 ሜትር የእግረኛ መንገድን ጨምሮ 50 ሜትር የጎን ስፋት ያለው ይህ መንገድ በሦስት ዋና ዋና የመንገድ መጋጠሚያዎች ላይ የትራፊክ ማሳለጫ ተሸጋጋሪ ድልድዮች ተገንብተውለታል። እነዚህም፡-



## 1ኛ. የቃሊቲ ማሰልጠኛ ቀለበት መንገድ አደባባይ

የቃሊቲ - ቱሉዲምቱ አደባባይ የመንገድ ፕሮጀክት ግዙፍነትን አጉልተው ከሚያሳዩ የግንባታ ገፅታዎች መካከል የቃሊቲ ማሰልጠኛ ቀለበት መንገድ መጋጠሚያ ላይ የተገነባው ይህ የመጀመሪያው ማሳለጫ ድልድይ 240 ሜትር ርዝመት አለው።

የማሳለጫ ድልድዩ የቀድሞውን የቀለበት መንገድ አደባባይ ሳይነካ በቁመት ከፍ ብሎ የተገነባ በመሆኑ የትራፊክ እንቅስቃሴውን ከማሳለጡ ባሻገር ለአካባቢው ገፅታም ልዩ ውበት የሚያላብስ ነው።

## 2ኛ. ጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታል ማሳለጫ ድልድይ

ይህ የማሳለጫ ድልድይ 90 ሜትር ርዝመት ያለው ሲሆን ከሥር ወደ አቃቂ ከተማ ለመግባትና ለመውጣት ሲያገለግል፤ ከላይ ደግሞ በቀጥታ ወደ ቱሉ ድምቱ እና ቃሊቲ አደባባይ በግራና ቀኝ የሚተላለፈውን የትራፊክ ፍሰት በሚገባ የሚያሳልጥ ነው።

## 3ኛ ጋሪ ድልድይ

ሦስተኛውና የመጨረሻው የትራፊክ ማሳለጫ ተሽጋጋሪ ድልድይ ቀደም ሲል ጋሪ ድልድይ እየተባለ በሚጠራው ሥፍራ ላይ የተገነባው ሲሆን 50 ሜትር ርዝመት እና 20 ሜትር የጎን ስፋት እንዲኖረው ተደርጎ በአዲስ መልክ የተገነባ ነዉ።

የዚህን መንገድ ግንባታ የቻይና ኮሚኒኬሽን ኮንስትራክሽን ካምፓኒ ከ2 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ ያከናወነው ሲሆን ኢንጂነር ዘውዱ አማካሪ ድርጅት ደግሞ የማማከርና ቁጥጥር ስራውን አከናውኗል።

# 3.የአውጉስታ - ወይራ መንገድ



በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ በተለምዶ አውጉስታ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ጀምሮ እስከ ወይራ ድረስ የተዘረጋው የአውጉስታ ወይራ መንገድ የከተማውን ማስተር ፕላን በጠበቀ መልኩ እንደ አዲስ ተገንብቶ ለአገልግሎት ክፍት ተደርጓል።

1.4 ኪሎ ሜትር ርዝመትና 20 ሜትር የጎን ስፋት ያለው ይህ መንገድ በሁለት አመት ተኩል ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ ለምረቃ በቅቷል።

መጋቢት 2012 ዓ.ም የተጀመረውን የዚህን መንገድ ግንባታ ቲኤንቲ ኮንስትራክሽን ከ308.3 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ ያከናወነው ሲሆን ኦሜጋ ኮንሰልቲንግ አማካሪ ድርጅት ደግሞ የማማከር እና የቁጥጥር ስራውን ተከታትሎታል።

ይህ መንገድ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እንደ አዲስ ከመገንባቱ በፊት በጣም ጠባብ እና ለእግረኛም ሆነ ለተሽከርካሪ ምቹ ያልነበረ ሲሆን አሁን ላይ እግረኛ መንገድ፣ የመንገድ መብራት እና ሌሎች የመንገድ መሠረተ ልማቶች ተሟልተውለት በመገንባቱ የተሻለ የትራፊክ ፍሰት እንዲኖር አስችሏል።

መንገዱ ከጦር ሀይሎች ወደ ቶታል የሚወስደውን ቀለበት መንገድ በመያዝ በአውጉስታ  ወደ ወይራ፣ ቤተል አደባባይ፤ እንዲሁም ከአውጉስታ በወይራ መጋጠሚያ ወደ ዘነበ ወርቅና አየር ጤና አደባባይ ለመሄድ አማራጭ መንገድ በመሆን የሚያገለግል ነው።

# 4.ከአፍሪካ ህንፃ-ጀሞ መስታወት ፋብሪካ መንገድ

በተለምዶ አፍሪካ ህንፃ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ጀምሮ እስከ ጀሞ መስታወት ፋብሪካ የሚደርሰው መንገድ 1.6 ኪ.ሜ ርዝመትና 20 ሜትር የጎን ስፋት ያለው ሲሆን ግንባታው በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የራስ ኃይል ነው የተከናወነው።

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚናገሩት መንገዱ እና የመንገዱ አካል የሆነው ድልድይ ከመገንባቱ በፊት ጠጠር የእግረኛ መንገድ ብቻ የነበረ ሲሆን በተለይ በክረምት ወቅት በጎርፍ የመጥለቅለቅ ችግር ያጋጥም ነበር።

በተለይ ደግሞ የጀሞ ወንዝ በሚሞላበት ወቅት ድልድይ ባለመኖሩ ለመሻገር ይቸገሩ እንደነበር የአካባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ። አሁን ግን  በአንድ በኩል መንገድ በመሰራቱ በሌላም በኩል ከ9ሜትር በላይ ርዝመት ያለው ድልድይ በመገንባቱ ችግራቸው እንደተቃለለ ይናገራሉ።

ይህ መንገድ ከአየር ጤና አደባባይ ወደ ጀሞ ሶስት መሄድ ለሚፈልጉ አሽከርካሪዎች ሚካኤል አደባባይ ሳይደርሱ የቀለበት መንገዱን የዳር መስመር በመያዝና ወደ ቀኝ በመታጠፍ በቀጥታ በጀሞ መስታወት ፋብሪካ በኩል ወደ ጀሞ ሶስት አደባባይ ለመውጣት ያስችላቸዋል።

በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ሥራዎች ኮርፖሬሽን አማካሪነት በባለስልጣኑ የራስ ሀይል መንገድ ግንባታ ሎት 1 በታህሳስ 2013 ዓ.ም የተጀመረው ይህ መንገድ ለግንባታው 94 ሚሊዮን 849 ሺህ 437 ብር ወጪ የተደረገበት ሲሆን ግንባታው ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቆ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።



# 5. የቁርቆስ ማርገጃ - ቡልጋሪያ መንገድ



የቁርቆስ ማርገጃ-ቡልጋርያ መንገድ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በራስ ሀይል የገነባው ሲሆን 1.16 ኪ.ሜትር ርዝመትና የእግረኛ መንገድን ጨምሮ 20 ሜትር የጎን ስፋት አለው፡፡

ግንቦት 2013 ዓ.ም የተጀመረው ይህ መንገድ ከቄራ ወደ ለገሃር እና ቁርቆስ ቤተክርስትያን እና ለገሃር አካባቢ መሄድ ለሚፈልጉ አሽከርካሪዎች በአቋራጭነት በማገልገል በአካባቢው ላይ ያለውን የትራፊክ ጫና ማቃለል ያስቻለ መንገድ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ሥራዎች ኮርፖሬሽን አማካሪነት በባለስልጣኑ የራስ ሀይል የመንገድ ግንባታ ሎት1 የተገነባው ይህ መንገድ 34 ሚሊዮን 898 ሺ 990 ብር ወጪ ሆኖበታል፡፡

መንገዱ የተገነባበት አካባቢ አዲስ አበባ ውስጥ ከሚታወቁ ገበያዎች አንዱ የሆነውን የቁርቆስ ገበያ እና ዝነኛውን የቁርቆስ ቤተ ክርስቲያን የሚያዋስን ከመሆኑ በተጨማሪ ተጠጋግቶ የሚኖር ከፍተኛ ቁጥር ያለው ነዋሪ ያለበት እንደመሆኑ ፋይዳው ከፍተኛ ነው፡፡

# ፮. ቤላ መንገድ -ፈረንሳይ ፓርክ- ፈረንሳይ - አቦ ቤተ ክርስቲያን መንገድ



ቤላ መንገድ- ፈረንሳይ ፓርክ ፈረንሳይ ኤምባሲ- አቦ ቤተክርስቲያን መንገድ ከ6 ኪሎ አደባባይ ወደ ፈረንሳይ ሌጋሲዮን አቅጣጫ ሲጓዙ በተለምዶ 05 ቀበሌ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገኘውን ቃኘው ሻለቃ አደባባይን እንዳለፉ ከፈረንሳይ ኤምባሲ ዋናው በር መግቢያ ዝቅ ብሎ ወደ ቀኝ በመታጠፍ መነሻውን ያደረገ መንገድ ነው፡፡

ይህ የፈረንሳይ ኤምባሲ- ፈረንሳይ ፓርክ -አቦ ቤተክርስቲያን የመንገድ ግንባታ ቃኘው ሻለቃ አደባባይ ሆኖ አሻግሮ ሲመለከቱ እንደ ሳር ውስጥ መንገድ በርቀት በቀጭኑ ይታያል፡፡

ከዚህ በፊት በቦታው አስፋልት መንገድ አልነበረም፤የአካባቢው ነዋሪዎችም በተለይ አቦ ቤተክርስቲያን እና አካባቢው የሚኖሩ ከተሜዎች ወደ መሀል ከተማ ለመምጣት ከፍተኛ 12 የሚገኘው ፈረንሳይ ማዞሪያ ድረስ የእግር ጉዞ ማድረግ ይጠበቅባቸው ነበር፡፡

አሁን ግን 1.2 ኪ.ሜ ርዝመትና 15 ሜትር የጎን ስፋት ያለው ፣ የመንገድ ዳር መብራትና የእግረኛ መንገድ የተሟላለት ባለ አንድ አቅጣጫ የአስፋልት መንገድ በመገንባቱ ችግራቸው ተረት ሆኖ ቀርቷል፡፡ <<ልጁን አንሺው ምጡን እርሺው>> ይባል የለ፡ ፡

የክረምቱን ጭቃ፣ የበጋውን ፀሀይ፣ ሌላው ቀርቶ ወላድ ምጥ ሲይዛት እንኳ የአምቡላስ መንገድ እጦታቸውን ረስተው ዛሬ ላይ ታክሲው ከበራቸው ላይ ቆሞ አራት ኪሎ… 6 ኪሎ… እያለ ሲጣራ ፤ ወይ ጊዜ- - - ጊዜ ደጉ ያስብላል፡፡

መንገዱ ከ6 ኪሎ እና ከሌሎች ቦታዎች ተነስተው ወደ ፈረንሳይ ፓርክ፣ ፈረንሳይ አቦ ቤተክርስቲያን እና አልፈው ወደ ጉራራ ኪዳነ ምህረት አካባቢ ለሚጓዙ አሽከርካሪዎች አማራጭና አቋራጭ መንገድ በመሆን የሚያገለግል ይሆናል፡፡

ጥር 2012 ዓ.ም የተጀመረው ይህ መንገድ 106 ሚሊዮን 91 ሺ 204 ብር ወጪ የሆነበት ሲሆን በኢትጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ኮርፖሬሽን አማካሪነት እንዲሁም በራስ ሃይል መንገድ ግንባታ ሎት 2 የተገነባ ነው፡፡

# 7. ናሳው ሪል ስቴት አርሴማ ቀለበት መንገድ



የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን በበጀት ዓመቱ ግንባታቸውን ካጠናቀቃቸው መንገዶች መካከል ከናሰው ሪል ስቴት ወደ አርሴማ ቀለበት መንገድ አንዱ ነው።

በ102 ሚሊዮን 329 ሺህ 7315 ብር የተገነባው ይህ መንገድ 1ነጥብ 2 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው ሲሆን የእግረኛና የብስክሌት መስመርን ጨምሮ 30 ሜትር የጎን ስፋት አለው።

አካባቢው መንገድ ያልነበረበትና ለእግረኛም ሆነ ለተሽከርካሪ የማያመች ኮረኮንች ስለነበር ምንም ዓይነት ትራንስፖርት ያልነበረበት በመሆኑ ነዋሪዎች ለዘመናት ሲቸገሩ ኖረዋል።

ጥቅምት 2013ዓ.ም ግንባታው የተጀመረው ይህ መንገድ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የራስ ኃይል መንገድ ግንባታ ሎት 4 የተገነባ ሲሆን የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ኮርፖሬሽን በአማካሪነት ተሳትፏል። መንገዱ ከመገንባቱ በፊት የነበረው ሁኔታ በተለይ በክረምት ወቅት ለመንቀሳቀስ አስቸጋሪ እንደነበረ የአካባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ።

መንገዱ ከጀሞ አንበሳ ጋራዥ አካባቢ በአርሴማ ቤተክርስቲያን በኩል ወደ ለቡ መብራት ለማቋረጥ አማራጭ መንገድ በመሆን ያገለግላል ።



## ፰. የቱሉ ዲምቱ ኮንዶሚኒየም መቃረቢያ አስፋልት መንገድ



የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን በስራ ተቋራጮች ካስገነባቸው በርካታ አቋራጭ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች መካከል የቱሉ ዲምቱ ኮንዶሚኒየም - የውጨኛው ቀለበት መንገድ ግንባታ ሌላኛው ተጠቃሽ ነው።

ግንቦት 2012 ዓ.ም በይፋ የተጀመረው ይህ የመንገድ ፕሮጀክት 1 ነጥብ 3 ኪሎ ሜትር ርዝመት እና 40 ሜትር የጎን ስፋት ያለው ሲሆን አሁን ላይ የአስፋልት ማንጠፍ፣ የእግረኛ፣ የመንገድ ዳር መብራት ተከላ ስራዎች ተጠናቀው የትራፊክ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

የግንባታ ስራውን ዲሪባ ደፈረሻ የተባለ ሀገር በቀል የስራ ተቋራጭ ያከናወነው ሲሆን የማማከርና የግንባታ ቁጥጥሩን ስራ ደግሞ ጎንድዋና አማካሪ ድርጅት ሲከታተለው ቆይቷል።

ለፕሮጀክቱ ግንባታ ማስፈጸሚያ ከ145 ሚሊዮን 211 ሺ 478 ብር በላይ ወጭ ተደርጎበታል።

# ፱. በሻሌ ኮንዶሚኒየም የውስጥ ለውስጥ መንገድ



የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን ለጋራ መኖሪያ ቤቶች የመንገድ መሰረተ ልማት በማቅረብ የነዋሪዎችንም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ትስስር ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል።

የግንባታ ስራው በየካቲት ወር 2013 ዓ.ም የተጀመረው የበሻሌ ኮንዶሚኒየም አስፋልት መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ተጠናቆ ለአገልግሎት ክፍት ተደርጓል።

3.5 ኪሎ ሜትር ርዝመትና ከ15 እስከ 20 ሜትር የሚደርስ የጎን ስፋት ኖሮት የተገነባው ይህ መንገድ በጥላሁን አበበ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ የግንባታ ስራው የተከናወነ ሲሆን ጎንት ኮንሰልቲንግ ኢንጂነርስ ደግሞ የማማከርና የቁጥጥር ስራውን ተከታትሎታል።

ለግንባታ ስራው ማስፈፀሚያ 370 ሚሊዮን 763 ሺ 331 ብር በላይ ወጪ ተደርጎበታል።

## ፲0.ዮናስ ሆቴል- ኬብሮን ፋርማሲ



በአዲስ አበባ ከተማ በቅርቡ ከተገነቡ በርካታ አቋራጭ መንገዶች መካከል ዮናስ ሆቴል- ኬብሮን ፋርማሲ መንገድ ይጠቀሳል፡፡

ከአድዋ አደባባይ ወደ መገናኛ የሚወስደውን ዋና መንገድ - በሃያ ሁለት አካባቢ ካለው የመንገድ ኔትወርክ ጋር በአጭር ርቀት ለማስተሳሰር የተገነባው የኬብሮም ፋርማሲ - ዮናስ ሆቴል መንገድ ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ራስ ሃይል መንገድ ግንባታ ሎት 2 ነው የተገነባው ፡፡

በተጨማሪም የመንገድ ግንባታና ጥገና ዲዛይን ክለሳ ትግበራና ክትትል ዳይሬክቶሬት በአማካሪነት የተሳተፈበት ይህ የውስጥ ለውስጥ መንገድ የእግረኛና የአስፋልት መንገዱን ጨምሮ በአጠቃላይ 540 ሜትር ርዝመት እና 15 ሜትር የጎን ስፋት ያለው ነው፡፡

ግንባታው ጥር 2016 ዓ.ም ግንባታው የተጀመረ እና ከ17ነጥብ2ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተገነባው ይህ መንገድ የአካባቢውን ነዋሪዎች የመውጫ እና የመግቢያ የመንገድ ችግር ከመቅረፋ በተጨማሪ ከሃያ ሁለት ወደ ሾላ ገበያና ተቃራኒ አቅጣጫ ለሚሄዱ አሽከርካሪዎች አማራጭ መጋቢ መንገድ በመሆን ያገለግላል፡፡

# 11.ማዘር ቴሬዛ ድልድይ



የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን የድልድይ መልሶ ግንባታ ካከናወነባቸው አካባቢዎች መካከል ማዘር ተሬዛ ተብሎ የሚጠራው ድልድይ ይገኝበታል።

ታህሳስ 2015 ዓ.ም ግንባታው የተጀመረውና ያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት አካባቢ የሚገኘው ይህ ድልድይ በጣም ጠባብ እና ረዘም ላለ ጊዜ አገልግሎት በመስጠቱ የተነሳ ለጉዳት የተዳረገ በመሆኑ በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ ቅሬታን ሲፈጥርም የቆየ ነበር።

ቀደም ሲል የነበረው ድልድይ ከብዙ ዓመታት በፊት በአካባቢው ህዝብ ዘንድ በበጎ አድራጎት ሥራው በሚታወቀው ማዘር ቴሬዛ ድርጅት አማካኝነት የተገነባ ሲሆን በእርጅና ምክንያት ላለፉት አሥር ዓመታት ከአገልግሎት ውጪ በመሆኑ በተለይም በክረምት ወቅት እግረኞች በአሮጌው ድልድይ ላይ ለመጓዝ ይቸገሩ እንደነበር የአካባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ።

ድልድዩ በእርጅና ምክንያት ተሽከርካሪን ማስተላለፍ ባለመቻሉ በሰፈራው ችግሮች ሲያጋጥሙ የህክምና አገልግሎት የሚሠጡ አምቡላንሶች እና የእሳትና ድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች ገብተው ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት አዳጋች እንደነበር ያስታውሳሉ።

ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ሙሉ በሙሉ ነባሩን ድልድይ በማፍረስ በ15 ሚሊዮን ብር ወጪ በአዲስ መልክ በራስ ሀይል የገነባው ድልድይ የነበረውን ችግር አቃሏል። ድልድዩ በ8 ሜትር የጎን ስፋት የተገነባ በመሆኑም ተሽከርካሪ በቀላሉ ማንቀሳቀስ አስችሏል።

# 12.በላይ ዘለቀ/አጣሪ/ ድልድይ



የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን በከተማዋ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ላይ የሚገኙና ለረጅም ዓመት አገልግሎት በመስጠት ጉዳት የደረሰባቸውን ድልድዮች በአዲስ መልክ መልሶ የሚገነባ ሲሆን ከነዚህም መካከል አጣሪ ድልድይ አንዱ ነው።

በጉለሌ ክፍለ ከተማ በተለምዶ በላይ ዘለቀ በሚባለው አካባቢ የተሰራው ይህ ድልድይ በክረምት ወቅት በአካባቢው ለማለፍ የነበረውን ችግር ያቃለለ ሲሆን መኖሪያቸው በጎርፍ ሲጎዳ ለነበሩ ነዋሪዎች እፎይታን የሰጠ ድልድይ ነው።

በጉለሌ ክፍለ ከተማ፣ በላይ ዘለቀ ትምህርት ቤት አካባቢ የሚገኘው የአጣሪ ድልድይ በአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን በራስ ኃይል የተገነባ ሲሆን ከወንዙ ጠለል በላይ በ7 ሜትር ከፍታ፣ 10 ሜትር ርዝመት እና 10 ሜትር የጎን ስፋት አለው።

ከ38ነጥብ5 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ ህዳር 2015ዓ.ም ግንባታው የተጀመረው ይህ ድልድይ በአሁኑ ወቅት ተጠናቅቆ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

# የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን የተሽከርካሪና መሣሪያዎች ጥገና ማዕከል



በአዲስ አበባ ከተማ ቃሊቲ አካባቢ በ47 ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ከ638 ሚሊየን 305 ሺ 804ብር ወጪ የተገነባው የተሽከርካሪና መሣሪያዎች ጥገና ማዕከል የመጀመሪያው ምዕራፍ የተጠናቀቀ ሲሆን ቀሪ የማጠናቀቂያ ሥራዎች በመሰራት ላይ ናቸው።

ግንባታው ታህሳስ 2015 ዓ.ም የተጀመረው ይህ የጥገና ማዕከል አንድ ዘመናዊ የጥገና ማዕከል ሊኖረው የሚገባውን ፋሲሊቲ አሟልቶ የያዘ ነው።

ማዕከሉ የያዛቸው ዋና ዋና ክፍሎች፦

•የተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎች የቴክኒክ ፍተሻ ማዕከል

•የነዳጅ ማከማቻና ማከፋፈያ ዴፖ፣

•የተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎች እጥበትና ግሪስ ማድረጊያ ማዕከል

•የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች የጥገና ማዕከል፣

•የቀላል ተሽከርካሪዎች ጥገና ማዕከል፣

•የከባድ ገልባጭ ተሽከርካሪዎች የጥገና ማዕከል /በአንድ ጊዜ እስከ 20 ተሽከርካሪዎችን የሚይዝ/፣

•የተሽከርካሪና መሳሪያዎች አካል ጥገና ማዕከል፣

• የሞተር ጥገና ማዕከል፣

•የተሽከርካሪና መሳሪያዎች አውቶ-ኤሌክትሪክ ጥገና ማዕከል /በአንድ ጊዜ እስከ 10 ተሽከርካሪዎችን የሚይዝ/፣

•የተሽከርካሪና መሳሪያዎች አካላት ማምረቻ ማዕከል፣

•የብረታ ብረት ማምረቻ ማዕከል፣

•የግንባታ ግብዓት ማምረቻ ፕላንቶች ጥገና ማዕከል፣

•የቀላልና ከባድ ተሽከርካሪዎች፣ የግንባታ መሳሪያዎች እንዲሁም የፕላንቶች መለዋወጫ ዕቃዎች ማከማቻ ግምጃቤት፣

•መለስተኛ ክሊኒክ እና

•የሠራተኞች የልብስ መቀየሪያ ክፍሎችን በውስጡ የያዘ ነው።

298 ወንድ እና 48 ሴት በድምሩ 346 ሠራተኞችና ባለሙያዎች ያሉት የጥገና ማዕከሉ 275 ቀላል ተሽከርካሪዎች፣198 ከባድ ተሽከርካሪዎች፣170 የግንባታ መሳሪያዎች፣13 የግብዓት ማምረቻ ፕላንቶች፣11 ሞተር ሳይክሎችን የሚያስተዳድር ሲሆን በተጨማሪም የመለዋወጫ ዕቃ ግዢ የመፈፀም፣በራስ ሀይል መቅረብ የማይችሉና በኪራይ ለሚመጡ ተሽከርካሪዎች ስፔሲፊኬሽን የማዘጋጀት ሥራዎችንም ያከናውናል።

የጥገና መዕከሉ በዘመናዊ መልክ መገንባት የተቋሙን የተሽከርካሪ እና ማሽነሪ ጥገና አቅም በማሳደግ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ዋነኛ ተልዕኮ የሆነውን የመንገድ ግንባታ ስራዎች በስኬት ለመፈጸም የሚያስችል ነው።

አድራሻ:- ሳር ቤት አደባባይ ፊት ለፊት

ስ.ቁ፡-+251113713400፣

+251113710877፣

ነፃ የስልክ መስመር፡- 8267

ፖ.ሳ.ቁ፡- 9206

ፋክስ፡- +251113712982

Email:- aacracom@gmail.com

የባለስልጣኑን መረጃዎችን በማህበራዊ ሚዲያዎቻችን ለመከታተል:-

https://www.facebook.com/AbabaCity

https://t.me/AddisRoads/

https://twitter.com/AbabaCity

https://www.instagram.com/addisababaroads/

https://www.tiktok.com/@addisababaroads

https://www.youtube.com/@addisababacityroadsauthori1369

ድረ ገፃችን

www.aacra.gov.et











join us

8267